# የወያኔን ቧልት ማስቆም ይቻላል

የሀገራችን አዛውንት ዝምታ ለበግም አልበጀት ይላሉ፡፡ ሀቅ ነው--ሲጨቆን ሲበደል ዝም ያለ ሕዝብ ዕጣው ዕድሉ ጭፍን ብዝበዛና ጨካኝ ጭቆና ይሆናል፡፡ ዝምታ ለሕዝብ ጠንቅ ነው፡፡ ጨዋነት አይደለም፡፡ ትዕግስትም ሊባል አይችልም፡፡ ጫንቃውን ለጭቆና ያመቻቸ ሕዝብ ብሎ ያስነቅፋል እንጂ፡፡
ትግል በስልት መሆኑ ግልፅ ቢሆንም ወያኔን በሁሉም መስክ በማጋለጥ በሕዝብ ላይ የሚያካ ሂደውን አሰቃቂ ቧልት ማስቆም ይቻላል፡፡ ወያኔን በድፍረትና በስፋት በማጋለጥ፡፡ ለምሳሌ ባዕድ ሀገሮች የመለስ ዜናዊ አጋር ሆነው በሕዝባችን ቁስል ላይ ጨው ነስናሽ ሆነዋል፡፡ እንግሊዝ ለምሳሌ የወያኔን የቀድሞ የፀጥታ (የአፈና) ተቋም መሪን ክንፈ ገብረመድህንና ሌሎችን ያሰለጠነች ናት፡፡ ለወያኔ ፖሊስ መኪናም መሳሪያም ለግሳለች--በእንግሊዝ በተለገ ሰ ላንድ ሮቨር የመጡ ፖሊሶች ናቸው አሰፋ ማሩን የገደሉት፡፡ የወያኔን መሐይም የፓርላማ አባላትን ዛሬ በአዲስ አበባ አሰልጣኝ የእንግሊዝ ካውንስል ነው፡፡ በ1997 የሕዝብን ትግል ከወኔ ቢስ የተቃዋሚ መሪዎች ነን ከሚሉ ጋር አብረው ያከሸፉት የአሜሪካና የአንግሊዝ ኤምባሲ ተጠሪዎች ናቸው፡፡ ዛሬ በአዲስ አበባ ያለው የእንግሊዝ አምባሰደር የኢትዮጵያ ሕዝብ የዛሬ መቶ ዓመትም ዴሞክራሲ አይገባውም ከማለቱ ሌላ የእንግሊዝ የእርዳታ ገንዘብ ለፓኪስታኖችና ሆዳም ወያኔዎች እንዲሆን እየጣረ ነው፡፡ ይህን ሁሉ ይፋ አውጥቶ ማጋለጥ ና የእንግሊዝን መንግስት በእንግሊዝ ሕዝብ ፊት ማሳጣት ይቻላል/ይገባል፡፡ በተለይ በሕዝበ ትግል አፈና ላይ ደጋፊ ሆነው ወያኔን ማጀባቸውን በስፋት ማጋለጡ አስፈላጊ ነው፡፡ የአሜሪካማ አይነሳ ነው፡፡ የአሜሪካ ሕዝብ ገንዘቡ ለአፋኝና ነፍሰ ገዳይ ቡድን እየተሰጠ መሆኑን ማወቅ ይኖርበታል፡፡ የወያኔን አፋኝ ወታደሮችና የስለላ መኮንኖች አሰልጣኝ አሜሪ ካም ናት፡፡ አሜሪካ በሀገራችን የጦር ሰፈር መሰረተች ሲባል ታዲያ ተቃዋሚዎች ከነመገናኛ ብዙሀናቸው ምነው ዝምታን መረጡ? ለወያኔ በሁሉም መስክ ድጋፍ በመሰጠትና የዴሞኮራ ሲ ትግሉን በማፈን መስክ አሜሪካ አሉታዊ ሚናዋ ከፍ ያለ ነው፡፡ ለዚህም ነው ከመቸውም ጊዜ በበለጠ በስፋትና በተባባረ መንገድ በአሜሪካ ከፍተኛ የማጋለጥ እርምጃ መወሰድ የሚገ ባው፡፡ የሰብዓዊ መብት ረገጣውንም ሙሉ በሙሉ የማያቀርቡትንም የባዕድ ተቋሞች-በተለ ይም አምኔሰቲና ህዩማን ራይትስ ዋች የተባሉትንም--በሚገባ መውቀሰ ያስፈልጋል፡፡

ይህ ሁሉ ይቅደም በሚል እንጂ የወያኔን አሳፋሪ ቧልት ለማስቆም በመጀመሪያ ደረጃ በግንባ ር መሰለፍ ያለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱ ነው፡፡ በቅድሚያ ታጋይና አታጋይ ነን የሚሉ ሀይሎች ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው በመገኘት የወያኔ መፎከሪያና መቀለጃ ከመሆን በተቻለ መጠን መከላከል መራቅ አለባቸው፡፡ ወያኔ በየጊዜው በሀሰት አቀነባባሪዎቹ አማካኝነ ት የሚያዘጋጃቸው ቅንብሮቹ መሳቂያ ሆነው ይቀሩ ዘንድ አንድም ለቧልቱ ትንሽም ቅንጣ

ትም ቢሆን መንደርደሪያ--መጠየቂያ አለመስጠት ሲገባ በሌላ በኩል ደግሞ መስክሮች አጋ ላጮች ብሎ በግድና በሀይል የሚኮለኩላቸውን በተመለከተም አስረኞች ላየ የሚደርሰውን ደፍሮ በስፋት ማጋለጡ አስፈላጊና ተገቢም ነው:: ግዳጅም ነው:: በወያኔ ተይዘው ስየል የተቀበሉ ሁሉ ይህንኑ ማጋለጥ መቻል አለባቸው:: በሀገር ቤት ላሉ ባያመች  እንኳን ወደ ውጭ የወጡ ምነዋ ስለደረሰባቸው ስየልና በደል ሁሌም አድብስብሰው ይቀራሉ? ለምን በዝርዝር አይናገሩም? ለምን እስረኛን አሰቃዮቹን የወያኔ ቅጥረኞች ስም ጠርተው አያጋል ጡም? ከወዲ ሻምበል ሌላ በከርቸሌና ቃሊቲ ሰው አልነበረም? የለም? በወያኔ እጅ ስቃይን መቀበል የሚያሳፍር ሳይሆን የሚያኮራና ለሀገር ለወገን የተከፈለ ዋጋ እንደመሆኑ መጠንም የሚያስመሰግን ነው:: ቅሌቱና ውርደቱ የወያኔ እንጂ የተጠቂው፤ ወይም ሰለባ የሆነው እስረ ኛ አይደለም:: ወያኔ የፖለቲካ እስረኞችን ሰብዕና ለመስበር በሚወስደው እርምጃ ሳንሳቀቅና ሳንሸማቀቅ ደፍሮ በመውጣት ማጋለጥ ለትግሉ ጠቃሚ ነው:: ዝምታው የሚጠቅመው ለወያኔ ነው:: ስለዚህ የዝምታው ግንብ መፍረስ መንኮታኮት አለበት:: በወያኔ እስር ቤት ስቃዩ ምን ነበር? ምንድነው? ማናቸው ገራፊዎቹ? ስየሉ ምንድነው? በኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ የቀረበ የስየል ዝርዝር በቅርቡ አንበናል:: በዚህ መሰረት ታስረው ተሰቃየን ብለው የተፈቱ እስረኞች ምነዋ ዝም አሉ? ስደተኞቹ በግፍ ና በሀይል ወደ ወያኔ ተመልሰው ሲሰጡና እነ ኢፖእአኮ ሲጮሁ ለምንስ ሌሎች ዝምታን መረጡ?

ወያኔን በአረመኔነቱ ብናጋልጠውና ዘመቻው ደግሞ በህያው ምስክሮች ቢታጀብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ውጤቱ ከፍተኛ መሆኑ አያጠራጥርም:: አሊያም ተይዘው ተሰቃዩ የተባሉት ጭራሽ አልተነኩም የሚባል ካልሆነ በስተቀር ዝምታው ለታዛቢ ግራ የሚያጋባ የሆነ ጉዳይ መሆኑ አልቀረም:: በእስረኛ እከሌ ላይ ይህ ደረሰ፤ ይኸው ራሱ ራሷም ምስክር ሆኑ ማለት መቻል አለብን :: ተሰቃዩ የተባሉት ዝምታን ካቀፉና አልፎም ባልተጠበቀ ደረጃ  ያለው የፖለቲካ እስረኛ ቁጥር ትንሽ ነው ብለው የዓይጥ ምስክር ድንቢጥ ዓይነት ለወያኔ ሽፋን ከሰጡ ነገር ሁሉ ተበላሸ  ማለት ነው:: መቸም ትላንት ታጋይና ፀረ ወያኔ ሆነው ለእስር የተዳረጉ ከወራት እስራት በኋላ በገዛ ፍቃዳቸው የወያኔ የገደል ማሚቴዎች ሆነው ሊንጫጩ መጠበቅ የለበትም:: ከተቀየሩ ምክንያቱ አንድም ተገዝተው ነው፤ ሌላም ስየል ደርሰባቸውና ፈርተው ሰግተውና ለጭንቀት ተዳርገው ነው ብሎ መገመት ይቻላል:: ሁሉም ሰው ስየልን እስከመጨረሻው ሊቋቋም ችሎታ የለውም:: ሊችልም አይጠበቅም:: ስለዚህም ከተመክሮአችን እንደምናውቀው በዱላና ደብድባና ስቃይ የተነሳ እስረኞች ሊሸነፉ ሊደክ ሙ ይችላሉ--ይህ ሁኔታም መጠበቅ አለበት:: ነገር ግን ከዚህ ሁሉ መከራ በኋላ ለስደት ዕድል ያገኙ ግን ዝም ማለታቸውና የደረሰባቸውን አለማጋለጣቸው ምንም ማጠየቂያ አይኖ ረውም::

ዝምታ ለወያኔ ያመቸዋል--ወንጀሉ ይደበቅለታል። አረመኔነቱ ይሸፈንለታል። ባዕዳን ደግሞ ጉዱን ወንጀሉን ቢያውቁም ወዳጃቸው ነውና ይደብቁለታል። በየጊዜው ወያኔ እስረ ኞችን --ባሕታዊን ሳይቀር--ጥፋተኛ ነን ብላቸሁ ፈርሙ ብሎ ካስገደደ በኋላ በዚሁ ድርጊ ቱ እንደሚያላዝንና እንደሚመፃደቅ ተመክሮ አሳይቶናል። ራሱ ወንጀሉን ፈፅሞ ይቅርታ ልጠየቅ ብሎ መድረቁንም ታዝበናል። የሰበራቸውንም እስረኞች የቀድሞ ጓዶቻቸውን በይ ፋ እንዲያወግዙ ያደርጋል። ይህንንም ስናይ ስንታዘብ የቆየነው ነው። ሚዛን አልባም ነው--በተዋከበ ሰው ስቃይ ላይ የተመሰረተ ፕሮፓጋንዳ ነውና። በ1997 የታሰሩት ያለፉት ሂደት ነው። በጋዜጠኞች ወዘተ ላይ ተደጋገሟል። ለዚህም ነው ዛሬ በስደት ያሉት ሰለባ ናቸው የተባሉት ግለሰቦቸ ደፈር ብለው ወጥተው ቦታና ስምንም ጠቅሰው ምስክርነት በመስ ጠት ወያኔን በይፋ ማጋለጥ ያለባቸው። ማጋለጡ ግዳጅ ነው። ያልነበረ ከሚያወራ የነበረ ቢመሰክር ይታመናል። ለዚህም ነው የወያኔን የቪዲዮ ልፈፋና ቧልት በአጭር ለመቅጨት ወንጀሉን ማጋለጥ ያለብን--አመኔታ ቅንጣትም እንዳይኖረው ለማድረግ።

እናስ ምን እናድርግ?

1. በወያኔ ተዋክበን፤ ታሰረን፤ ተሰቃይተን የሚሉ በስደት ያሉ ዜጎች የወያኔን ወንጀል በዝር ዝር ያቅርቡ፤ ምስክርነት ይስጡ፤ የገራፊና አሰቃዮቹን ስም ይዘርዝሩ ያጋልጡ፤
2. ወንጀለኛ ወያኔዎችን የሚያውቁ አጓጉል ምስጢር ጠባቂ ሳይሆኑ ወንጀለኞቹን በዓለም አቀፍ ደረጃ ያጋልጡ፤
3. በወያኔ ግፍ ስቃዩን አልችል ብለው የተገኙትም ሳያፍሩና ሳይሸማቀቁ ያልሆነ ምስክርነት የሰጠነው፤ ለወያኔ የተሸነፍነው በዚህ በዚህ ምክንያት ነው ብለው ለምህረት ሰጪው ሕዝብ ይናገሩ፤ያጋልጡ
4.በዓለም አቀፍ መድረኮች ሁሉ ለወያኔ ፀረ ሕዝብነት እኔ ምስክር ነኝ ብለው የደረሰባቸውን ሁሉ ይተርኩ፤
5. ዜጎች ሁሉ ምዕራባውያን ለወያኔ እየሰጡ ያሉትን ድጋፍ በሁሉም መስክ በቁጣ ይቃወሙ ፤ ያጋልጡ
6. በወያኔ ላይ ማዕቀብ የተባለውን ያጥብቁ እንጂ የወያኔን እንጀራ፤ ቢራ፤ ወይን ወዘተ መነገድና ከወያኔ በተጨባጭ መተባባር ያቁሙ። ፀረ ወያኔው ማዕቀብ ይጠናከር፤

ዋናው ተልዕኮ ግን ወያኔን በቆራጥነት አምርሮ ታግሎ ከስልጣን ማስወገድ ነውና በትግላችን ለወያኔም ለባዕዳንም ተጨባጭና መራራውን ትምህርት መስጠት ይጠበቅብናል። ቻይናውም ፤ ህንዱም፤ አረቡም፤ ወያኔውም ሁሉም በሀገራችን ሲጫወትና በንቀት ሲሰድበንና ሲበዘብዝ

ን በዝምታ ማየቱና መስማቱ ቀርቶ እስመቼ ውርደት በሚል ገሞራዊ ንዴት በነዚህ በዝባዥ ችና በቅጥረኛው በወያኔ ላይ በመነሳትና በማጥቃት ሀገርን ማስከበር ይገባናል። ወያኔም ባዕዳኖቹም ንቀውናል--ይህን መገንዘብ አለብን። ለምን? በዝምታ ጭቆናን ስለምንቀበል። ዝምታ እስከመቼ? ውርደትንስ እስከመቼ ልንችል ልንሸከም?

የሀገር ጥሪ ተነስ አምፁ የሚል ነው። ጆሮአችን ለዚህ ጥሪ አንጂ ለሌላ ውዥንብር ክፍት አይሁን ! በየአቅጣጫው በወያኔና ባባዕድ ደጋፊዎች ላይ ጥቃት እናድርስ ። የአገዛዙ ዕድሜ መጨረሻው ደርሷልና መዳኛ መንገድ ሳንከፍትለት እናጥቃው። ባዕዳን የሕዝብን ድል ለመንጠቅ እያደረጉ ያሉትን ሴራ እናክሽፍ። ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን እንወጥር። አስመሳዮ ችና አወናባጆችን እናርቅ።

እንባችንን ማበሻ ሆነ በደላችንን ማስወገጃ መፍትሂው የወያኔን፤ የመለስን አገዛዝ በትግል ማቾነፍና ማስወገድ ብቻ ነው።
ፀረ ወያኔው የሕዝብ ትግል ይፋፋም!